# የሰብአዊ  መብት ሥራዎችን ማፈን፤

## የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ሕግ በኢትዮጵያ ውስጥ ያስከተለው ተጽዕኖ

የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በስራቸው ላይ ገደብ በሚጥለው ህግ የተነሳ ክፉኛ ተዳክመዋል። በርካታዎቹ ድርጅቶቻቸው የተመሰረቱባቸውን አላማዎች ትኩረት ለመቀየር ተገደዋል፤ እንቅስቃሴያቸው ተቀንሷል፣ ጽሕፈት ቤቶች ተዘግተዋል፤ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞችም ሥራቸውን አጥተዋል። የሁለት ግንባር ቀደም የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ከ 1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር  በላይ የሚሆን ገንዘብ እንዳይንቀሳቀስ ታግዷል።

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት አዋጅ በጥር ወር 2009 ዓ.ም. ነው የታወጀው። አዋጁ ለሰብአዊ መብት ተግባራት በሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ከፍትኛ ገደቦችን ይጥላል፣ በድርጅቶቹ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል ከልክ ያለፈ ሥልጣን ለመንግስት ይሰጣል፣ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሰላባ የሆኑ ሰዎችን ደኅንነት ለከፋ አደጋ ያጋልጣል፣ እንዲሁም የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ለእስር እንዲዳረጉ ይፈቅዳል።

መንግስት ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ያለውን የጠላትነት ስሜት እና የሰብአዊ መብት ተግባርንም የህግ አግባብ እንዳለው ስራ እንደማይቆጥር ለበርካታ ዓመታት የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን ለማያቋርጥ ወከባ፣ እስራት፣ እና ክስ በመዳረግ አሳይቷል። ህጉ ይሄው የፍርሃት ዳመና ተቋማዊ መልክ እንዲይዝ አድርጓል። አብዛኛዎቹ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች በአሁኑ ሰዓት ሃሳባቸውን ለመግለጽ ይሰጋሉ።

አዋጁ የኢትዮጵያን ሕዝብ መብቶች መከበርና መረጋገጥ በሚመለከት አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል። ባሁኑ ሰአት የሰብአዊ መብቶች መከበርን አስመልክቶ መንግስትን ተጠያቂ የማድረግ አቅም ያለው አንድም ድርጅት የለም ማለት ይቻላል።

ይህ ህግ ሰዎች በነጻነት ሃሳብን በንግግርና በጽሁፍ ለመግለጽና በመንግስት ላይ ትችቶችን ለመሰነዘር እንዳይችሉ ገደብ ከሚያስቀምጡት ከ2008 በኋላ ከወጡት ሶስት ሕጎች  አንዱ ነው። መንግስት በሚወስዳቸው እርምጃዎች ላይ የሚደረጉ ክትትሎች ጨርሶ በተመናመኑበት በዚህ ሁኔታም የኢትዮጵያ መንግስት የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በስፋት መፈጸሙን ቀጥሏል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያ መንግስት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አዋጅን እንዲያሻሽል፤ በሰብአዊ መብት ተግባራት ላይ የተጣሉትን ገደቦች እንዲያነሳ፣ እጅግ አስፈላጊ ለሆነው የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች  ስራ ተገቢውን እውቅና እንዲሰጥ፣ እንዲያከብርና፣ እንዲያስከብር ይጠይቃል።

amnesty.org

የመግለጫው መለያ: AFR 25/002/2012
መጋቢት 2012

AMNESTY INTERNATIONAL




# የሰብአዊ መብት ሥራዎችን ማፈን፤

## የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ሕግ በኢትዮጵያ ውስጥ ያስከተለው ተጽዕኖ

AMNESTY
INTERNATIONAL

አምነስቲ ኢንተርናሽናል አለም አቀፋዊ ንቅናቄ ሲሆን ከ3 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ደጋፊዎቹ፣ አባላቱ እና ተሳታፊዎቹ በ150 አገራት እና ግዛቶች ውስጥ አስከፊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ረገጣዎች እንዲቆሙ በመታገል ላይ ይገኛሉ።

አላማችን ለእያንዳንዱ ሰው በአለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ እና በሌሎች አለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች መመዘኛዎች የተጠበቁት መብቶች ሁሉ እንዲከበሩ ነው።

ከማንኛውም መንግስት፣ ፖለቲካዊ አመለካከት፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወይም ኃይማኖት ገለልተኛ ስንሆን ገቢያችንን በዋናነት የምናሰባስበው ከአባላት መዋጮና ከገለልተኛ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሚገኙ እርዳታዎች ነው።

**AMNESTY**
**INTERNATIONAL**

በመጀመሪያ እ. አ. አ. 2012 ዓ. ም. በአምነስቲ ኢንተርናሽናል ታተመ
Amnesty International Ltd
Peter Benenson House
1 Easton Street
London WC1X 0DW
United Kingdom

© የአምነስቲ ኢንተርናሽናል እትመት 2012

የመግለጫው መለያ፡ AFR 25/002/2012 Amharic
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ የተተረጎመ
በአምነስቲ ኢንተርናሽናል የታተመ፤ ኢንተርናሽናል
ሴክሬታሪያት፣ዩናይትድ ኪንግደም

ሁሉም ያሳታሚው የባለቤትነት መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው።
የዚህ ህትመት የቅጂ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው በማናቸውም
መንገድ ይህን እትመት በማባዛት ያለክፍያ ግንዛቤ ለማስጨበጫነት፣
ለቅስቀሳ እና ለማስተማሪያ አገልግሎቶች እንዲውል መጠቀም
የሚቻል ሲሆን በሽያጭ መልክ ማሰራጨት የተከለከለ ነው።
ህትመቱ ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት አላማዎች ከዋለ፣ የህትመቱን
ጠቀሜታ መገምገም ይቻለው ዘንድ ተጠቃሚዎቹ እንዲያሳውቁት
አሳታሚው ይጠይቃል። ከተጠቀሱት ውጭ በሌላ ማንኛውም
ሁኔታዎች ወይም ለሌላ እትመት አገልግሎት ለመጠቀም ወይም
ለመተርጎም ወይም ለማሳተም በቅድሚያ የአሳታሚው በጽሑፍ
የተረጋገጠ ፈቃድ ያስፈልጋል፤ እንዲሁም ክፍያም ሊጠይቅበት
ይችላል።

ፈቃድ ለመጠየቅ ወይም ለማንኛውም ተጨማሪ መረጃ
የሚከተለውን አድራሻ ይጠቀሙ። copyright@amnesty.org

የሽፋን ምስል። በ2009 በወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት
አዋጅ የተካተቱት ድንጋጌዎች በሰብአዊ መብት ድርጅቶች የገንዘብ
አቅምና እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ገደብ ይጥላሉ።
© Amnesty International

amnesty.org



# ለመርዳት እፈልጋለሁ

**አምነስቲ ኢንተርናሽናል** በከፍተኛ ሁኔታ በሚታወቁ ግጭት ያለባቸው ሥፍራዎችም ሆነ በተረሱ የአለማችን ክፍሎች ፍትሕ፣ ነጻነት እና ተገቢው ክብር ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲሆን ቅስቀሳ የሚያደርግ ሲሆን የተሻለ ዓለምን ለመገንባት የሚያስችል የሕዝብ ተሳትፎ እንዲኖርም ያበረታታል።

## ምን ማድረግ ይኖርብዎታል?

በመላው አለም የሚታዩት ሕዝባዊ እንቅስቃሰዎች የሚያሳዩት ሰብአዊ መብቶችን የሚያኮስሱ አደገኛ ኃይሎችን ማስቆም የሚቻል መሆኑን ነው። የእዚህ እንቅስቃሴ አካል ይሁኑ። ፍርሃትንና ጥላቻን የሚዘሩትንም ይታገሏቸው።

- ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጋር አብረው በመቆም የሰብዓዊ መብቶች እረገጣ እንዲያከትም የሚካሄደው አለም ዓቀፍ ንቅናቄ አካል ይሆኑ። ለውጥ እንድናመጣ ይደግፉን።
- የአምነስቲ ኢንተርናሽናልን ሥራ ለማገዝ እርዳታዎን ይለግሱ።

## ተባብረን ድምጻችን ተሰሚ እንዲሆን ለማድረግ እንችላለን።

☐ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል አባል በመሆን ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ፍላጎት አለኝ

ሥም

አድራሻ

አገር

ኢ-ሜል

☐ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል የገንዘብ እርዳታ ማድረግ እፈልጋለሁ (የገንዘብ እርዳታው በፓውንድ፣ በአሜሪካ ዶላር ወይም በዩሮ ሊሆን ይችላል)

የገንዘቡ መጠን

ከሚከተለው ካርዴ ተከፋይ ይሁን ቪዛ ☐ ማስተር ካርድ ☐

የካርድ ቁጥር

የአገልግሎት ጊዜው ማብቂያ

ፊርማ

ይህን ቅጽ ከሞሉ በኋላ በሚገኙበት አገር ለሚገኝ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጽ/ቤት ያስረክቡ።

የሌሎች የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጽ/ቤቶችን አድራሻ ለማግኘት፡
www.amnesty.org/en/worldwide-sites
በሚኖሩበት አገር የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጽ/ቤት ከሌለ ቅጹን በሚከተለው አድራሻ ይላኩ፡

**Amnesty International**, International Secretariat, Peter Benenson House,
1 Easton Street, London WC1X 0DW, United Kingdom

amnesty.org